# የአውሮፓ ነዋሪ ኢትዮጵያዊያን ጥያቄ የመላው ሕዝባችን ጥያቄ ነው!!

April 8, 2009

## ከማስተዋል አወቀ

የመጀመሪያው የሰው ፍልሰት መነሻ የኢትዮጵያ መሬት መሆኑን ትተን የዛሬው ዘመነኛው ትውልድ ፍልሰት ብንመለከት ካለፋት አርባ አመታት ጀመሮ ኢትዮጵያዊያን የማንኖርባቸው የዓለም ክፍሎች በጣም ጥቂት መሆናቸው ግልጽ ነው። የዚህ ሁሉ ፍልሰት መነሻው የሀገራችን የረጋ የፖለቲካ ስርዓት አለመኖር የፈጠረው ችግር መሆኑ የታወቀ ነው። አሁንም ሁኔታው ባለመስተካከሉ የተነሳ ያልወጣው ለመውጣት የማያደርገው ጥረት የለም። የወጣው አይመለስም ምን አይቶ ይመለሳል መንስ ይጠብቀዋል።በቦሌ ተደግሶለት ከተሸኘው ጅምሮ በባሌ፤በሀረር፤ በጎንደርና በሞያሌ የሀገራችን ጠረፎች ነብሱን በጨርቁ ቋጥሮ በእግሩ ኳትኖ ሶማሊያ፤ ሱዳን፤ኬንያ፤ጅቡቲ፤ ግብጽና የመን የገባውን ቀዳማዊ የዘማናችን ስደተኛ "ሀ" ብለን በእነዚህ ሀገሮች አሸጋጋሪነት ወደ አሜሪካ ካናዳ አውስትራሊያ ኤሽያና አውሮፓ የፈለሰው ኢትዮጵያዊ ቁጥር ቀላል አደለም።

ይህ ሁሉ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ዛሬ ከጥቂት የአቶ መለስ ዜናዊ ጥቅም ተቋዳሾች በስተቀር ያለምንም የፆታ፤የሀይማኖትና የቋንቋ ልዩነት የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት ቢኖረውም ሀገር ቤት የሚኖረው ሕዝብ ብሶትና መከራ በጋራ ይሰማዋል። የሕዝቡ በችግር፤ መጎሳቀል፤ መራቡ፤ መጠማቱ የመኖር ዋስትናው መመናመኑ አሁንም ሰላም ይነሳዋል። በተለይም የሀገሪቱ ብሄራዊ ደህንነትና ሉዓላዊነት ላይ የወያኔ አገዛዝ የሚከተለው የተንሸዋረረ አረማመድ በፍጹም የሚደገፍ ጉዳይ አይደለም።እንደዚሁም በፖለቲካ አመለካከታቸው የተነሳ ለተገደሉ፤ለተገረፉ፤ ለተንገላቱ፤ ለታሰሩ፤ብሎም ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ በተጨማሪ በሥራ ሂደታቸው ዋስትና ያጡ ወገኖች የሰቆቃቸው መንስኤ የሆኑ የወንጀሉ ፈጻሚና አስፈጻሚዎች ሁሉ በነጻ ፍርድ ቤት እንዲዳኙና ለፈጸሙት ጭፍጭፋ ተገቢ የሆነ ፍርድ እንዲያገኙ ይጠይቃል።

የሀገራችን ሕዝብ እነዚህን ጥያቄዎች በነጻ እንዳያነሳ በአባገነኑ መለስ ዜናዊ ቡድን ታፍኖአል።ስለሆነም የዚህ ትውልድ ድምጽና ትክክለኛ የፖለቲካ ስሜቱ መግለጫ ከአፈሙዝ ራቅ ብሎ በነጻነት የሚንቀሳቀሰው፤ በውጭ ሀገር የሚገኘው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ነው። ለዚህም ነው የአባገነኑ መንግስት መሪና የቡድኑ አባላት በሚንቀሳቀሱበት ነጻው አለም የተቃውሞ ማእበል የሚንጣቸውና የሚያሸብራቸው።የታደሉት ሀገራት መሪዎች ወደ ውጭ ሲወጡ መጡልን ብሎ በሰልፍና በድግስ የሚቀበላቸው የየሀገራቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ የሌላው አለም ሳይቀር እልል ብሎ አቀባበል ሲያደርግላቸው መመልከት ዛሬ ለእኛ ኢትዮጵያዊያን የሚያስቀና እና የተናፈቀ ነገር ከሆነ ከግማሽ ምእተ አመታት በላይ አስቆጠረ።

ሁኖም ግን ምን አይነት አመራር የሚሰጡ መሪዎች ናቸው ለዚህ የታደሉት ብሎ መጠየቅ ደግሞ ተገቢ ነው። ለመሆኑ የነአቶ መለስ አገዛዝ ሰዎች እስከመቼ ነው በየሄዱበት እየባነኑ የሚኖሩት? የስጋት፤ የውርደት፤ የሀፍረትና የደብቁኝ ኑሮ የማይሰማቸው ለምንድን ነው? ለምንድን ነው ስጋቱ በርታ ባለበት ቦታ ሁሉ በብረት አጥር ሽቦ እና በተሽከርካሪ ብረት ለበስ መሳሪያ የሚታጀቡት? ይህ በሌለበት ቦታ ደግሞ ለእለት ሆዱ ባደረ ደረት ሰፊና ቁመተ ቀውላላ የጸጥታ ዘበኛ ተከበው የሚኖሩት? እውን የኢትዮጵያ ህዝብ ጨካኝና አሳዳጅ ስለሆነ ነው? እውነታው ይህ ሳይሆን አቶ መለስና ቡድናቸው በየለቱ የሚገሉት ወገን

የሕሊና ሰላምና የህዝብ ጥላቻ እንዲኖር ስለአደረጉ ነው። ይህንን መሻር የሚችለው ጥላቻ የፈጠረው አገዛዝ ብቻ ነው ይኸውም መፍትሄው ከህዝብ ጋር መታረቅ ነው። የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ከሀገራቸው አልፈው በሰሞኑ የአውሮፓ ሕዝብ ለእርሳቸው ያሳይው ፍቅር ምን ያህል እንደሆነ መመልከት በቂ ነው።

ኦባማ በዚሁ ጉብኝታቸው ለደጋፊያቸው ሰላምታ ሲሰጡ ካላት ፍቅር የተነሳ እራሷን መቆጣጠር ተስኖአት ዘላ የሳመቻቸውን ወጣት አውሮፓዊ አቶ መለስ ሲመለከቱ ምን ተሰምቷቸው ይሆን? በተቃራኒው እሳቸው በየደረሱበት የበሰበሰ እንቁላልና ቲማቲም የተወረወረባቸውንና እየደረሰቻቸው ያለውን ውግዘት አስታውሰው አወዳድረውት ይሆን? እንደገና ወደ ባራክ ኦባማ ልመለስና በአውሮፓ ጉብኝታቸው ከተጠየቁት በርካታ ጉዳዮች መካከል አንዱ ፕሬዚዳንት በመሆንዎ የሚጸጽተወ ነገር አለ ወይን ተብለው ነበር የተጠየቁት? በሰጡትም ምላሽ ከሁሉ በላይ የሕዝብ አገግሎት እንደሚያረካቸውና በዚህም እንደሚደሰቱ አውስተው ነገር ግን አሉ እንደ ድሮው ያለጥበቃ በነጻነት ወተው ለመግባት አለመቻላቸውን ነበር ፕሬዚዳንት በመሆናቸው ካጡት ነገር በምሳሌነት ያወሱት። ታዲያ መለስስ ይህ እንዴት ተሰምቶአቸው ይሆን ብለን መጠየቅ ይኖርብል። በእርግጥ መልሱ የሳቸው ቢሆንም አወዳድሮ ማየቱ ህሊና ላለው የሚጠቅም እንጅ የሚጎዳ አይደለም።

አቶ መለስ ይህንን እያዩ በቁም እየባነኑ በየቀኑ የቁም ሞት ከመሞት፤ ሞትን አሸንፎ ለታሪክ ፍርድ መቅረብ፤ እራስን ለበደሉት ሕዝብ በይፋ አጋልጦ መታረቅና የህሊና ነጻነትን ከአካል ነጻነት ጋር ደርቦ ማግኘት፤ ወይም ሞትን እየሸሹ ተደብቆ አይቀሬ ሞት መሞት።

ምርጫው የአቶ መለስና የዳረጎት ተሳታፊዎቻቸው የተግራይ ፤የአማራ፤ የኦሮሞ የደቡብ ድርጅት ጥርቃሞ ኢህአዴግ የሚባለው የጎጠኖች ስብስብ ባለስልጣናት ይሆናል።

ይህን ፎቶ ተመልከቱት ያለየለት ባለዛር መስልው እንዴት የለንዶን ሰልፈኞችን  ሲመለከቱ



የኢትዮጵያ ገዝዎች ይህን ለማለትና እራሳቸውን ከሕዝብ ጋር  ለማስታረቅ የሚያስፈልጋቸው ቆራጥ ውሳኔ የሰሩትን ወንጀል ለማረም በግልጽ በመቅረብ ብሄራዊ እርቅና ብሄራዊ ስሜትን እና ጥቅምን ማዳበር የበደሉትን ለመካስ መንነሳት፤ የኅጠኝነት ከፋፍለህ ግዛ ዘዴ መመሪያቸውን ማቆም የመሳአሉትን እርምጃወች መውሰድ ነው።

የሀገሪቱ የምጣኔ ሀብት ለማሳስደግ ሁሉም በሀገሩ እኩል የመስራትና ጠተቃሚ የሚሆንበትን መርህ መከተል ይጠይቃቸዋል።እነዚህ ሁሉ የተጠራቀሙ የፖለቲካ ጭቆናዎች ናቸው የሕዝባችን ሰላም የነሱት፡ አብሮ በሀገሩ ጸንቶ እንዳይኖር ሰላሙን በመንሳት ለችግርና ለተጎሳቆለ ኑሮ የዳረጉት።ሀገራችን ሳታጣ ያጣች ።ሳትደሕይ የደኸየች የአስተዳደር በደል ቀፍድዶ ለችግር የደረጋት።በአለም መድረክ ብርቱ ሰራተኛ ሕዝብ እንደሌላት ሁሉ ለከፋ ቸነፈር ተዳረገች፤አንደኛው የሀገሪቱ ክፍል ለምርት ተስማሚ እንኳን ባይሆን በሌላኛው ማቻቻል ሲቻል ይህን ከማድረግ ይልቅ የልመና ኮረጆን አንጠልጥሎ በየፈረንጁ ሀገር በር ላይ መቆም ተለመደ ።ልመና ከመዘውተሩ አልፎ  እንደ ሕጋዊ መብት በልበ ሙሉነት እና በድፍረት የሚለምኑ ከሀገራችን አልፈው አፍሪካን የሚወክሉ ለማኝ ግኾዎች አፍርትን ቁጭ አልን። አያሳፍርም ማፈር ብቻ ሳይሆ ያሳቅቃል።

ብዙ ሀገራት አያሌ የተፈጥሮ ፈተና ይገጥማቸዋል። የቻይናን ኅርፍ ፤ የአሜሪካን የንፋስ አመታዊ ማእበል የሳይቭሪያን በረዶ በትንሹ መመልከት ይቻላል ይህን ሁሉ ተቋቁመው ከሀገራቸው አልፈው እኛ ኮፋዳ ይዘን እንለምናቸዋለን የአሁኑማ ልማና ከማስፈራራት ጋር መደባለቁን ባለፈው ሳምንት  መለስ ዜናዊ

በለንደኑ የአፍሪካ የእርዳታ ጉዳይ አስመልክቶ ከቻናል አራት ጋዜጠና ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ባትመጸውቱን ወዮላችሁ በማለት ሲያስጠነቅቁ ሰማሁና የለማኝ ደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ የተባለውን አስታወሰኝ።የኛ የመለመኛ የየመመቱ ምክንያት ግን ድርቅ ነው። ሀገራችን ርቀን የምንገኘው ወገኖች ስለድርቁ ሌላው አለም ያለ ግምት እኮ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እግዜብሄር የከዳት ዝናብ የሚባል ጠብ የማይልባት ። ለመስኖ የሚውል ውሃ ሳይሆን የሚጠጣ እንኳ የሌላት፤ በተፈጥሮ የተበደለች ሀገር እንደሆነች ነው የሚከራከሩንና የሚነግሩን።

በእነርሱ መፍረድ ከባድ ነው የሚሰማቸው ምን ያርጉት በየቴሌቭዥን የሚያዩ ምስል ይህንኑን የሚያጎለምስ ነው።እውነታውን የሚያውቁት ደግሞ የለመና ድርጅት አቋቁመው መደበኛ ሥራ ስለአደረጉት እንዴት አርገው እውነቱን ይናገሩ ያስተባብሉ ባለቤቱ ያላደረገውን ከእነሱ ምን እንጠብቃለን። ሀገራችን ከዳር እስከዳር ለምናውቅ ግን የሚያበሳጭ ሌት ቀን እንቅልፍ የመነሳ ጉዳይ ነው።ምክንያቱም ሳናጣ ያጣን ሆነን በመቅረባችን ነው።

አቶ መለስ ከታች በበለጸጉ ሀገራት መሪዎች የእራት ግብዣ ላይ ተገኝተው የሆኑትን በስእሉ ብቻ ማየት ይቻላል።



ሰሞኑን በእንግሊዝ ሀገር ለንዶን በተደረገው 20 የበለጸጉ ሀገራት መሪዎች ጉባኤ ላይ የአፍሪካን የልመና ኮሮጆ ይዘው ምጽዋእት እንዲጠይቁ የተላኩት መለስ ዜናዊ ለንዶንን ከረገጡ ጀምሮ ሀገሪቱን ለቆው እስከሚወጡ ድረስ በኢትይዮጵያዊያን የደረሰባቸው ውግዘትና ነቀፌታ ቢያንሳቸው እንጅ የበዛባቸው አይደለም።መለስ አገዛዛቸው በሰብአዊ መብት ጥሰት በጭፍጨፋና በዘር ማጥፋት ወንጀል በኤርትራና በሶማሌ ዜጎች ሳይቀር ተወግዘዋል። የበደኖ፤ የአርባጉጉ፤ የጋምቤላ፤ የጎንደር ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ምእመናን፤ የአዲስ አበባ ሰላማዊ ሰልፈኞች እና የኦጋዴን ሰላማዊ ሕዝብ ደም ሲፋረዳቸው ሰነበተ።በቅጥረኝነት ሶማሌ ውስጥ ያፈሰሱት ደም አሁንም ሲጮህባቅቸው መጋፈጥ ተስኖአቸው እንዲሸማቀቁ ሆነ።ገና ነገ ለፍርድ ይቀርባሉ ፍርዱ ቢቻል በሀገረ ኢትዮጵያ ካልሆነ በሄጉ ችሎት የመቅረባቸው ቀጠሮ እየተቃረበ መምጣቱ የማይቀር መሆኑንም የአለማቀፉ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተከታታዬ ድርጅት ክስም የቀረበው በዚሁ የጉባኤ ሰሞን በሆኑን መለስንና ግብረ በሎቹን ያሸማቀቀና ያስደነገጠ ተጨማሪ ጉዳይ ነው። ያገሬ ሕዝብ ምንድን ነው ያለው “ሰርጥቆ ከማሰብ እጅን መሰብሰብ፣”

ታዲያ መለስ በየሄዱበት ከምስጋና ይልቅ ወቀሳና ነቀፌታ የዘወትር ምሳቸው ቢሆንም ሕዝብን በማራቆት እሳቸውና ተባባሪዎቹ የእለት ትኩስ እንጀራ እየበሉ ያሉ

ሕሊና ቢስ ገኸሮዎች ናቸው። መለስ ሕጻናትን፤ አዛውንቶችን እና ሰላማዊ ሕዝብን በጥይት እያነታጠረ ግባር ግባራቸውን የሚመታ አውሬ ሰራዊት አሰማርተው ወላጆች፤ ቤተሰብ፤ወዳጅና ዘመድ ብሶታቸውን እንኳ እንዳይገልጹ ገድበው ፤ የእሳቸው ልጅ የ2ኛ ደረጃ ትምሕርት ስትጨርስ የመመረቂያ ደስታ በሸራተን ሆቴል ደግሰው የጨፈሩ ሰብአዊ ፍጡርነታቸው የሚያጠያይቅ ሕሊና የተሸከሙ ጨካኝና አረመኔ አስተሳሰብ የተላበሱ ፍጡር ናቸው።

የኢትዮጵያ ወላጆች ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ልከው ወደ ቤታቸው ሳይመለሱ በአጋዚ እና በየቦታው ባሰማሯቸው የጸጥታ ሰዎች የጥይት እራት ሲሆኑ ወይዘሮ አዜብ መስፍን ከባላቸው ጋር የልጃቸውን  ደስታ በድግስ አጅበው አለማቸውን ቀጩ። እንደነሱ ልጅ ሁሉ በየሜዳው የጥይት ሰለባ ሆነው የወደቁት ልጆች  ደስታቸውን እንጂ መከራቸውን ለማየት የማይፈልጉ የሚንሰፈሰፉላቸው አባትና እናት ነበሯቸው። ግን በጨካኝ ግለሰቦች እጅ ወደቁ ይህንን እያወቁ አቶ መለስና ወይዘሮ አዜብ ግን በእነሱ ሬሳ ላይ ጨፈሩበቸው የአርበኝነትና የጀግና ውሎ ውለው በልጃቸው ድግስ አሳረጉት።

ይህ የጭካኔ ሥራቸው ነው በየሄዱበት እየተከተለ፤ ክብርና ሞገሳቸውን እየገፈፈ የሚያሸማቅቃቸው ።የለንዶኑ ኢትዮጵያዊያን ሰላማዊ ሰልፍ ጠያቂዎችም ይህን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች ነው ያንሱት።ጥያቄው ለማቅረብ ያልቻለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያ ቄ መሆኑን ተረድቶ  ቀኑ ሳይመሽ ወቅታዊ መልስ መስተት ያሸዋል ።

ሰልፈኞቹ ይዘውት የወጡት በስደት በሚኖሩባቸው አገሮች የገጠማቸውን በደልና የመዋህድ ችግር አቶ መለስ ብሄራዊ ስሜት ኑሮአቸው እንዲታደጉላቸው ለየሀገራቱ መሪዎች ድምጻቸውን እንዲያሰሙላቸው አይደለም። ተቆርቋሪ የህገር መሪ ያላቸው ዜጎች እኮ እንዲህ አይነት ጥያዜ የማቅረብም መብት ነበራቸው።

ግን እንኳን ራቅ ብለን በጠላትነት የተመደብነውን ይቅርና በየቀኑ የሚቦጠቡጡትን ዜጋ እንኳ መብት የማያከብሩ ናቸው በመሆኑም ከእርሳቸው ምን ተጠብቆ ነው ይህን ጥያቄ ስደተኛው የሚያቀርበው። ይልቁን በአውሮፓ ያሉት ወገኖቻችን ጥያቄ የመታደግ ጥያቄ አይደለም። በባህሪው ከዚህ በራቀና በሀገር ቤት የአቶ መለስ አገዛዝ በህዝቡ እያደረሰ ያለውን በደል እንዲያቆሙ፤የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ ፤የጭቆና አገዛዛቸው እንዲያከትም፤ እራሳቸውን ጭምሮ ወንጀለኛ ባለስልጣናት ለፍርድ እንዲቀርቡ፤ የፕሬስ ነጻነትን፡ የመደራጀትን፤ የመናገርን፤ የመሳሰሉት ነፃነቶች እንዲያከብሩ፤የህግ የበላይነትን እንዲኖር የጠየቁ ሰልፎች ነበሩ የተደረጉት።መለስ በአካል በተገኙበት ከተደረገው ሰልፍ በተጨማሪ ከአውሮፓ ራቅ ብለው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንም እንደዚሁ የሻማ ምሽት በማዘጋጀት ያስተላለፉት መልክት ተመሳሳይ አላማ የያዘ የአቶ መለስ መንግስት መልስ ሊሰጥበት የሚገባ ትያቄ ነው።




የአውሮፓ ነዋሪ ኢትዮጵያዊያን በለንደን ካደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ መካከል።

ከጉባኤው መጠናቀቅ በኃላ አቶ መለስ ጋዜጣዊ መግለጫ ይሰጣሉ ተብሎ በእቅድ የተያዘው መግለጫ በፍርሀትና በስጋት ተሰረዘ።መለስ በምን አንደበትወና  በየትኛው ሀቅ ነው ይህንን ነጻ አልም ጥያቄና መልስ የመጋፈጡት ? እርሰወ በጥይት ሲገሉ ሰላማዊ ሕዝብ ደግሞ በየቀኑ በሚያነሳው ሀቅ እየገደለወት ነው። ስንት ጊዜ ይሞቱ ይሆን? አገዛዘወ የህዝብን ጥያቄ ፈርቶ እስከመቸ መደበቅ ይቻለዋል? እንደለመዱት የእርሰወ የቁም እስረኛ የሆኑትን የማስታወቂ ሚኒስቴር ጋዜጠኞች መብት ገፈው የእርሰወን ዲስኩር ብቻ የሚያንቆረቁሩበትን አደንቋሪ መዝሙረወትን ወደ ሚያሰሙበት ኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና፡ ራዲዮ መድረክ ሂደው መግለጫ ሰጡ።እዚያም ቤት ቢሆን አፍነው ስለያዙት እንጂ ነጻ መድረክ ቢያገኝ እንዴት እርቃነወትን እንደሚገፈው ፕሬዚዳንት ሆነው ለኢትዮጵያ ህዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰጡት ቃለምልልሰ  የገጠመወትን መቋቋም አሁንም አይረሱትም። የጋዜጠኛ ጉዳይ ሲነሳ  የተዳፈነ እሳት ላይ መቆመወትን ለአንድ አፍታ እንኳ እንዳይዘነጉት ያስተነቀቀ መለክት ነው በአውሮፓ አግኝተው የተመለሱት።የሰጡትንም ጋዜታዊ መግለጫ ተከታተልኩት አንድም ስለደረሰበው ውርደት አልተነፈሱም። አወ ማን ተዋርጃለሁ ብሎ ይናገራል ያውም ከአባገነን? ዘበት ነው ከእርሰዎ አፍ ይህን መስማት አይታሰብም። ባይሆን ቴስታ ጥይት ግን ትጥቀወትን ፈተው ነበር።ባይሆንማ በለንደን የስ አት እላፊ ያውጁና በኢባሲ ታጣቂነት ተጠማሪ እንደአዲስ አበባው አደባባይ ለንዶንንም በደም ያጨማልቁት ነበር። ምን ያደርጋል ሳይሆን ለወ ቀረ።በነገር አቀባዮች በኩል ገን ቢያንስ የሰልፈኛውን ዝርዝር እንደደረሰወ ሰለሚገባኝ ፎቶገራፉን እያዩ ይደሰቱ እለወታለሁ።

ከዚህ ሁሉ መሸማቀቅ ይልቅ አገዛዘወትን ልክና ስርአት እንዲይዝ ማድረጉ አይበጀውትም? እራሰወትን አስረው ሌላውን ከማሰቃየት ስርአቱን ሰብአዊ ስሜት እንዲኖረው፤ ተጠያቂነትን መሰረት ያደረገ፤የሚገዙትን ታላቅ ሕዝብ ስሜትና ፍላጎት የሚጋራ ለንዶን ላይ ያሸማቀቀወ ሀፍረት ኢትዮጵያ ውስጥ ሊሰማወ ይገባል።ያፈሰሱትና አሁንም እያፈሰሱት ያለው ደም ምን ጊዜም ሊፋረደወ እንደሚችል ላይታ እንኳን እንዳይረሱት የአውሮፓ ነዋሪ ኢትዮጵያዊያን ጥሩ ትምህርትና የማስጠንቀቂያ ደወል ያስተላለፉ መሆኑን እንዲያውቁ ብቻ ሳይሆን ሳይወል ሳያደርትር አገዛዘወት ለኽት ኑሮት ለጠፋው ጥፋት እርምት የሚወስዱበት ወቅት ነው። እንደተለመደው ተግባረወ በማጭበርበርና በመከፋፈል የሚሸፍኑት ጉዳይ አይደለም። እጅግ በጣም ስር የሰደደ መፍትሄ የሚጠይቅ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ነው። ህዝቡ ቀኑ ሳይመሽ፤ ሳይውል ሳያደር ከአቶ መለስና

**ከአገዛዙ ተገቢ መልስ ይጠበቃል። የአውሮፓ ነዋሪ ኢትዮጵያዊያን ጥያቄም የመላው ኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄ ነው።**

ይህንን ፅሁፍ አስመለክቶ ለፀሀፊው የሚሉት ካለ: Tsegaye@solidaritymovement.org